# Tdap ክትባት

## ማወቅ የሚገባዎት

(ቴታነስ, Diphtheria እና Pertussis)

Many Vaccine information Statements are available in Spanish and other languages. See www.immunize.org/vis

Hojas de información sobre vacunas están disponibles en español y en muchos otros idiomas. Visite www.immunize.org/vis

## 1 መከተብ ለምን አስፈለገ?

**ቴታነስ፣ diphtheria እናpertussis** በጣም ከባድ በሽታዎች ናቸው። Tdap ክትባት ከእነዚህን በሽታዎች ሊከላከልልን ይችላል። እና ለእርጉዝ ሰዎች የሚሰጥ Tdap ክትባት የተወለዱ ህጻናትን ከ pertussis ይከላከላል።

**ቴታነስ** (Lockjaw) በአሁኑ ሰዓት ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በጣም አልፎ አልፎ የሚገኝ ነው። የጡንቻ መሸማቀቅን እና መወጣጠርን፣ ብዙ ጊዜ በሰውነት ሁሉ ላይ ይፈጥራል።

- በራስ እና በአንገት ላይ ያሉ ጡንቻዎችን በማሸማቀቅ አፍ መክፈትን፣ መዋጥን ወይም አንዳንድ ጊዜ የመተንፈስ ችግርን ያመጣል። በጣም ጥሩ የሆነ የጤና እርዳታ አግኝተው እንኳን ቴታነስ ከ 10 ሰዎች 1 ሰው ይገድላል።

**DIPHTHERIA** ም በአሁኑ ሰዓት ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በጣም አልፎ አልፎ የሚገኝ ነው  በጉሮሮ ጀርባ ወፍራም ቅርፊት እንዲፈጠር ያደርጋል።

- የመተንፈስ ችግር፣ የልብ ድካም፣ ፓራላይዝድ መሆን እንዲሁም ሞት ሊያስከትል ይችላል።

**PERTUSSIS** (Whooping Cough) ከባድ ሳልን ሲያመጣ ይህም የመተንፈስ ችግርን፣ ማስመለስን እና የእንቅልፍ መረበሽን ያስከትላል።

- ክብደት መቀነስን፣ የሽንት መቆጣጠር ችግር እና የጎድን አጥንት ስብራቶች። Pertussis ከተያዙ ከ 100 ህጻናት 2 ልጅ እና ከ 100 አዋቂዎች 5 ሰው በሽታው ይከፋባቸዋል፣ ይህም ወደ ኒሞኒያ ሊያደርስ ወይም ለሞት ይዳርጋቸዋል።

እነዚህ በሽታዎች የሚከሰቱት በባክቴሪያ ነው። Diphtheria እና pertussis ከሰው ወደ ሰው የሚስፋፋው ከማሳል ወይም ከማስነጠስ በሚወጡ ምራቆች ነው። ቴታነስ ወደ ሰውነት የሚገባው በተቆረጡ ቦታዎች፣ በጭረቶች እና በቁስል በኩል ነው።

ክትባት ከመምጣቱ በፊት በየዓመቱ 200,000 የ diphtheria፣ 200,000 የ pertussis እና በመቶዎች የሚቆጠሩ የቴታነስ ክስተቶች ሪፖርት ተደርገዋል። ክትባት ከጀመረ በኋላ የቴታነስ እና የ diphtheria ክስቶች በ 99% የቀነሱ ሲሆን የ pertussis ክስተት ደግሞ በ 80% ቀንሷል።

## 2 Tdap ክትባት

Tdap ክትባት ታዳጊዎችንና አዋቂዎችን ከቴታነስ፣ diphtheria እና pertussis ይከላከላል። የTdap አንድ ክትባት የሚሰጠው 11 ወይም 12 ዓመት ለሆነው ልጅ ነው። ይህንን እድልያላገኙሁሉ Tdap ን ቶሎ መከተብ አለባቸው።

Tdap የበለጠ ጠቃሚ የሚሆነው ከ 12 ወር በታች ከሆኑ ህጻናት ጋር የቅርብ ንክኪ ከሚኖራቸው ለጤና እንክብካቤ ሰጪ ባለሙያዎች ነው።

እርጉዝ የሆኑ ሴቶች የ Tdap ክትባትን **በየ እርግዝናው**የሚወለደውን ልጅ ከ pertussis ለመከላከል መውሰድ አለባቸው። ጨቅላዎች ከ pertussis ለሚመጣ ከባድና ህይወትን አደጋ ውስጥ ለሚጥል መወሳሰብ ተጋላጭ ናቸው።

Td የሚባል ሌላ ክትባት ከቴታነስና ከ diphtheria ይከላከላል፤ ከ pertussis ግን አይከላከልም። የ Td ቡስተሮች በየ 10 ዓመቱ መሰጠት አለባቸው። ከዚህ በፊት Tdap ወስደው የማያውቁ ከሆነ Tdap ልክ እንደ እነዚህ ቡስተሮች ሊሰጥ ይችላል።  ቴታነስ ኢንፌክሽንን ለመከላከል ከከባድ መቆረጥ ወይም መቃጠል በኋላ ሊሰጥ ይችላል።

ሃኪምዎ ወይም ክትባቱን የሚሰጥዎ ሰው የበለጠ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላል።

Tdap ከሌሎች ክትባቶች ጋር አብሮ ያለ ምንም ችግር ሊሰጥ ይችላል።

## 3 አንዳንድ ሰዎች ይህንን ክትባት መውሰድ የለባቸውም

- ከዚህ በፊት ከወሰደው ከ diphtheria፣ ቴታነስ ወይም pertussis ክትባት የተነሳ ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል አለርጂ ተነስቶበት የሚያውቅ ወይም ከየትኛውም የዚህ ክትባት ክፍል ጋር ከባድ አለርጂ ያለበት፣ Tdap ክትባትን መውሰድ የለበትም።  ክትባቱን ለሚሰጠው ሰው ያለብዎትን ከባድ አለርጂዎች ይንገሩት።
- በልጅነቱ ከ DTP ወይም DtaP ክትባት፣ ወይም ከዚህ በፊት ከወሰደው Tdap ክትባት የተነሳ በ 7 ቀን ውስጥ የተደጋገመ ሲዠር ወይም ራስን መሳት ያጋጠመው ሰው ካለ ከክትባት ሌላ መንስኤ ካልተገኘ በቀር Tdap መውሰድ የለበትም። Td ን ግን መውሰድ ይችላሉ።
- እነዚህ ካጋጠሙዎት ሃኪምዎን ያናግሩ፡
  - ሲዠር ወይም የነርቭ ስርዓት  ችግር ካለዎት፣
  - ከ diphtheria፣ ቴታነስ ወይም pertussis  ክትባት በኋላ ከባድ ህመም ወይም እብጠት ካለ፣
  - Guillain-Barré Syndrome (GBS) የሚባል በሽታ ኖሮብዎት የሚያውቅ ከሆነ,
  - ለክትባት በተቀጠረው ቀን ጥሩ ስሜት ካልተሰማዎት።



U.S. Department of Health and Human Services
Centers for Disease Control and Prevention

## 4 ስጋቶች

ክትባትን ጨምሮ በሁሉም መድሀኒቶች የጎንዮሽ ጉዳት የመፈጠር እድል አለ። እነዚህ መለስተኛ ሲሆኑ በትንሽ ቀናት ውስጥ በራሳቸው የሚጠፉ ናቸው። ነገር ግን አልፎ አልፎ ቢሆንም በጣም ከባድ ህመም ሊፈጠር ይችላል።

Tdap ክትባትን የወሰዱ አብዛኞች ሰዎች ምንም ችግር አያጋጥማቸውም።

Tdap ተከትሎ **መለስተኛ ችግሮች**
(ድርጊቶች መካከል ጣልቃ አልገቡም)

- ክትባቱ የተሰጠበት ቦታ ህመም (ከ 4 ታዳጊዎች 3 ወይም ከ 3 አዋቂዎች 2)
- ክትባቱ የተሰጠበት ቦታ መቅላት ወይም ማበጥ (ከ 5 ሰው 1)
- 100.4°F የሚደርስ መለስተኛ ትኩሳት((ከ 25 ታዳጊዎች 1 ወይም ከ 100 አዋቂዎች 1)
- ራስ ህመም (ከ 10 ሰው 3 ወይም 4)
- ድካም (ከ 3 ወይም 4 ሰው 1)
- ማቅለሽለሽ፣ ማስመለስ፣ ተቅማጥ፣ የሆድ ህመም (ከ 4 ታዳጊዎች 1 ወይም ከ 10 አዋቂዎች 1)
- መንቀጥቀጥ፣ የመገጣጠሚያ ህመም (ከ 10 ሰው 1)
- የሰውነት ህመም (ከ 3 ወይም 4 ሰው 1)
- ሽፍታ፣ የእጢዎች ማበጥ (ያልተለመደ)

Tdap ተከትሎ **መካከለኛ ችግሮች**
(ድርጊቶች መካከል ጣልቃ ገብተዋል ነገር ግን የጤና ክትትል አልፈለጉም)

- ክትባቱ የተሰጠበት ቦታ ህመም (ከ 5 ወይም 6 ሰው 1)
- ክትባቱ የተሰጠበት ቦታ መቅላት ወይም ማበጥ (ከ 16 ታዳጊዎች 1 ወይም ከ 12 አዋቂዎች 1)
- 102°F በላይ የሆነ ትኩሳት (ከ 100 ታዳጊዎች 1 ወይም ከ 250 አዋቂዎች 1)
- ራስ ህመም (ከ 7 ታዳጊዎች 1 ወይም ከ 10 አዋቂዎች 1)
- ማቅለሽለሽ፣ ማስመለስ፣ ተቅማጥ፣ የሆድ ህመም (ከ 100 ሰው 1 ወይም 3)
- ክትባት የተሰጠበት እጅ ጠቅላላ ማበጥ (ከ 500 ሰው 1)

Tdap ተከትሎ **ከባድ ችግሮች**
(የተለመዱ ተግባሮችን ማድረግ አለመቻል፤ የጤና ክትትልን የሚፈልጉ)

- ክትባት የተሰጠው ቦታ ላይ እብጠት፣ ከባድ ህመም፣ መድማት እና መቅላት (በጣም አልፎ አልፎ)

**የትኛውንም ክትባት ከወሰዱ በኋላ የሚያጋጥሙ ችግሮች፡**

- ከህክምና በኋላ፣ ክትባትን ጨምሮ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን ይስታሉ። ለ15 ደቂቃ መቀመጥ ወይም መተኛት ራስን መሳት፣ እንዲሁም በመውደቅ የሚመጣውን ጉዳት ይከላከላል። የድንዛዜ ስሜት፣ የእይታ ለውጥ ወይም ጆሮ ውስጥ ማቃጨል ከተሰማዎት ለሀኪምዎ ይንገሩ።
- አንዳንድ ሰዎች ትከሻ ላይ ከበድ ያለ ህመም ሲሰማቸው የተወጉበት እጃቸውን ማንቀሳቀስ ያስቸግራቸዋል። ይህ አልፎ አልፎ የሚከሰት ነው።
- የትኛውም መድኃኒት ከበድ ያለ የአለርጂክ አፀፋዊ ምላሽ ሊያስነሳ ይችላል። ከክትባት የሚያመጡ አለርጂኮች በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሲሆኑ ከአንድ ሚሊዮን ክትባቶች በ 1 ይገመታል።

ልክ እንደ ሌላው መድኃኒት፣ ክትባት በጣም ከባድ ጉዳት ወይም ሞት የሚያስከስትበት በጣም ጠባብ እድል አለ።

የክትባቶች ደህንነት ሁልጊዜ በቅርብ ክትትል ውስጥ ነው፡ ፡ ለበለጠ መረጃ ይህን ይጎብኙ፡ **www.cdc.gov/vaccinesafety/**

## 5 አደገኛ የሆነ የአለርጂ ምልክት ቢኖርስ?

**ማየት ያለብኝ ምንድነው?**

- ስጋት የሆነብዎትን ነገር እንደ ከባድ የአለርጂክ ምልክት፣ ከፍተኛ ትኩሳት ወይም ያልተለመዱ ባህርያትን ይመልከቱ።
- የከባድ አለርጂክ ምልክቶች የሚያካትቱት ሽፍታዎች፣ የፊትና የጉሮሮ እብጠት፣ የመተንፈስ ችግር፣ ፈጣን የሆነ የልብ ምት፣ መደንዘዝ እና ድካም ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ ከክትባት በኋላ ከትንሽ ደቂቃ እስከ ትንሽ ሰዓታት ይፈጠራሉ።

**ምን ማድረግ አለብኝ?**

- ከባድ የሆነ የአለርጂክ ምልክት ወይም ሊቆይ የማይችል አስቸኳይ ከመሰልዎት 9-1-1 በመደወል አቅራቢያዎ ወዳለው ሆስፒታል ይሂዱ። ካለበለዚያ ሀኪምዎ ጋር ይደውሉ።
- ከዚያ በኋላ የአለርጂው ምልክት ለ "Vaccine Adverse Event Reporting System" (VAERS) መመልከት አለበት፡ ፡ ሃኪምዎ ይህንን ፋይል ሪፖርት ማድረግ አለበት ወይም እርስዎ ራስዎ የ VAERS ድረ ገጽን በ **www.vaers.hhs.gov**በመጠቀም ወይም በ **1-800-822-7967**. መደወል ይችላሉ።

VAERS የህክምና ምክር አይሰጥም።

## 6 The National Vaccine Injury Compensation Program

የ National Vaccine Injury Compensation Program (VICP) የፌደራል ፕሮግራም ሲሆን በክትባት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ካሳ የሚሰጥ ነው።

በክትባት ጉዳት እንደደረሰባቸው የሚያስቡ ሰዎች ስለ ፕሮግራሙ ለማወቅ እና መጠየቂያ ለመሙላት በ **1-800-338-2382** ይደውሉ ወይም የ VICP ድረ ገጽን በ **www.hrsa.gov/vaccinecompensation**. ይጎብኙ። የካሳ ጥያቄ ለመጠየቅ የጊዜ ገደብ አለው።

## 7 እንዴት የበለጠ ማወቅ እችላለሁ?

- ሀኪምዎን ይጠይቁ። እርሱ ወይም እርሷ የክትባቱን ማብራሪያ ወረቀት ወይም ሌላ የመረጃ ምንጬን መጠቆም ይችላል/ትችላለች።
- የእርስዎ ግዛት የጤና ዲፓርትመንት ጋር ይደውሉ።
- Centers for Disease Control and Prevention (CDC) ን ያግኙ፡
  -**1-800-232-4636** (**1-800-CDC-INFO**)ይደውሉ ወይም
  - የ CDC ን ድረ ገጽ በ **www.cdc.gov/vaccines** ይጎብኙ

Vaccine Information Statement
# Tdap Vaccine - Amharic

Office Use Only

2/24/2015

42 U.S.C. § 300aa-26

Translation provided by Minnesota Department of Health